# <u>በረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ ከሰብዓዊ መብት የሲቪክ ድርጅቶች የቀረበ አስተያየት</u>

## 1. <u>መግቢያ</u>

በሰሜን ኢትዮጵያ ሲካሄድ የቆየውን ጦርነት ለመቋጨት በተደረገው የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት መሠረት፣ በጦርነቱ ለተፈፀሙ ብርቱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና የጦር ወንጀሎች ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም በሃገሪቱ የተከሰቱ ውስብስብ ግጭቶችና ቁርሾዎችን በዘላቂነት ለመፍታት ያለመ ረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር ተዘጋጅቷል።

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅቱ የተከናወነው ቀደም ሲል የሽግግር ፖሊሲ አማራጮችን የሚያብራራ ሰነድ (Green paper) ቀርቦ እና በውይይት ዳብሮ፣ በመቀጠልም የሽግግር ፖሊሲ አማራጮችን እንዲያጠና በተቋቋመው የጥናት ቡድን አማካኝነት በርካታ ህዝባዊ ውይይቶች ከተካሄደ በኋላ ነው። በነዚህ ውይይቶች የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችም ተሳትፈው፣ በፖሊሲ አማራጮቹ ላይ ያሏቸውን አስተያየቶች በተለያዩ መድረኮች ማቅረባቸው ይታወሳል። የጥናት ቡድኑ ስራውን ካጠናቀቀ በኋላም የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የማርቀቁ ስራ በፍትህ ሚኒስቴር ባለሙያዎች ተከናውኖ፣ ረቂቅ ፖሊሲውን በሚመለከተ በተዘጋጀ የፓወርፖይንት ሰነድ ላይ መለስተኛ ውይይቶች ተካሂደዋል። ነገር ግን የተሟላ ረቂቅ የሽግግር ፖሊሲ ሰነድ ለህዝብ ይፋ ተደርጎ ውይይትና ትችት አልቀረበበትም። የፓወርፖይንት ሰነዱም ቢሆን አስቀድሞ ለተወያዮች ደርሶ አስተያየት እንዲሰጡበት አልተደረገም። ረቂቅ የሽግግር ፖሊሲ ሰነዱ ለህዝብ ይፋ ስላልሆነ፣ ይህ አስተያየት የቀረበው በፓወር ፖይንት ተዘጋጅቶ በቀረበው ማብራሪያ ላይ ነው።

## 2. <u>ረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ለህዝብ ይፋ ሆኖ ግብረመልስ ሊሰጥበት የሚገባ ስለመሆኑ</u>

ከላይ እንደገለጽነው፣ የሽግግር ፍትህ ረቂቅ ፖሊሲው እስካሁን ለህዝብ ይፋ ባይደረግም፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንደሚፀድቅ መረጃዎች በመውጣት ላይ ይገኛሉ። ነገር ግን ረቂቅ ፖሊሲውን በሚመለከት ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ለጋሾች ጋር ከተደረጉ አጫጭር ውይይቶች በስተቀር በቂ ውይይት አልተደረገም። ሰነዱ ይፋ ስላልሆነ ደርዝ ያለው አስተያየት ለመስጠትም ዕድል አልተገኘም። ስማችን ከዚህ በታች የተዘረዘረው የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችም፣ ረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ሰነዱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ከመፅደቁ በፊት ለህዝብ ይፋ ተደርጎ በባለድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጥበት በአፅንኦት እንጠይቃለን።

በዚህ ረገድ በሽግግር ፍትህ አማራጮች ላይ ሰፊ ውይይቶች መካሄዳቸውን በበጎ የምንወስደው ቢሆንም፣ በፖሊሲ ዝግጅቱ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ እንደምንገኝ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ በረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ በቂ እና ፍሬያማ ውይይት እንዲደረግ አስቀድሞ ረቂቅ የፖሊሲ ሰነዱ ለህዝብ ይፋ እንዲሆን እንጠይቃለን። ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተጨማሪ፣ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን፣ የእምባ ጠባቂ ተቋም፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ምሁራን እና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ሰነዱን በዝርዝር ተመልክተው ከመፅደቁ በፊት አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ ዕድል እና በቂ ጊዜ ሊሰጥ ይገባል። ይህን ማድረግም ለፖሊሲ ሰንዱ ጠቃሚ ግብዓት ከማስገኘት በተጨማሪ፣ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው በህዝብ ዘንድ የተሻለ ተቀባይነት እና ተፈጻሚነት እንዲኖረው ለማድረግ ያግዛል ብለን እናምናለን።

## 3. <u>ለሽግግር ፍትህ ፖሊሲው አፈጻጸም መንግስት ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ግዴታውን ሊወጣ የሚገባ ስለመሆኑ</u>

በርካታ የአገራችን ክፍሎች ባሁኑ ወቅት በማያባራ ግጭት ውስጥ ይገኛሉ፣ የቀሪዎቹም ፀጥታ አስተማማኝ ሁኔታ ላይ ነው ያለው ለማለት ያስቸግራል። በአማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች በብዙ ቦታዎች ግጭቶች በሃገር መከላከያ ሰራዊት እና በፋኖ እና የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት ታጣቂዎች መካከል እየተካሄዱ ነው። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ያለው የፀጥታ ሁኔታ የተረጋጋ ቢመስልም፣ ምርጫ እስካሁን ለማካሄድ አልተቻለም። በጋምቤላም እንዲሁ በቅርብ ጊዜያት በትጥቅ የተደገፉ ግጭቶች ታይተዋል። በትግራይ ነፍጥ ያዘለ ግጭት ባይኖርም፣ ጦርነቱ የፈጠራቸው ቀውሶች ገና በቂ መፍትሔ አላገኙም፣ የፕሪቶሪያውን ስምምነት አተገባበር በተመለከተም በርካታ ቀሪ ጉዳዮች አልተፈቱም። በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለው ጥርጣሬ፣ የጥላቻ እና የመራራቅ ስሜት ገና አልበረደም።

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው በሃገሪቱ ዘላቂ ሰላም እና መተማመን ለማምጣት በጎ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ቢታመንም፣ አሁን ያለው የሃገሪቱ የፀጥታ ሁኔታ ካልተሻሻለ፣ መንግስትም ህግና ስርዓት የማስከበር ግዴታውን በአግባቡ ካልተወጣ በስተቀር የሽግግር ፍትህን ተግባራዊ ለማድረግ በጣም አዳጋች ይሆናል። አገሪቱ ውስጥ የሚታየው የግጭት አዙሪት እና ፈር የለቀቀ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ለብሔራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ከፍተኛ ተግዳሮት እንደሆነው ሁሉ ለሽግግር ፍትህ አፈፃጸምም እንቅፋት እንዳይሆን፡ መንግስት የህግ የበላይነትን ሊያረጋግጥ፣ የሰብዓዊ መብትቶች የማክበርና የማስከበር የፖለቲካ ቁርጠኝነት ሊኖረው ይገባል።

ይህን የምንለው፣ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋማት በተደጋጋሚ ባወጧቸው መግለጫዎች እንዳመለከቱት፣ በኦሮሚያ ዜጎች በታጠቁ ኃይሎች ሲታገቱ፣ ሲገደሉ እና ደብዛቸው ሲጠፋ በተጨባጭ መንግስት በቂ ዕርምጃ ሲወስድ ባለመታየቱ ነው። አንዳንድ የክልሉ እና የአካባቢ መስተዳደር የፀጥታ ኃይሎች ዜጎችን ሲያስሩ፣ ሲገድሉ እና አካላዊ ሰቆቃ ሲያደርሱ ይህን ለማረም መንግስት በተጨባጭ ዕርምጃ ሲወስድ፣ ወስዶም ከሆነ ለህዝብ ሲያሳውቅ ያልሰማን በመሆኑ ነው። በአማራ ክልል በበርካታ ቦታዎች በታጣቂ ኃይሎች የሚፈፅሙትን የሽምቅ ጥቃት ተከትሎ በግልፍተኝነት በሲቪሉ ህዝብ ላይ ጅምላ የበቀል ዕርምጃ የወሰዱ የመከላከያ ሠራዊት አባላት በተጨባጭ ተጠያቂ ሲደረጉ አለመሰማቱ፣ ድርጊቱን ከማውገዝ አንስቶ ለማስቆም እና ለመከላከል መንግስት ተግባራዊ ዕርምጃ ሲወስድ አለመታየቱ፣ በድሮንና ከባድ መሳሪያዎች ጥቃት ሲቪሎች ላይ የሚደርሰው ጉዳት እየባሰ መምጣቱ፣ ለግጭቱ አባባሽ ምክንያቶች ጭምር ሆኖ ስለሚታይ ነው።

ከዚህም አልፎ፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶቹን መርምሮ ይፋ የሚያደርገው መንግስታዊ ተቋም (ኢሰመኮ) ላይ ጭምር በአንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት የሚሰነዘሩ ማስፈራሪያ መሰል ንግግሮች ህዝብ በሂደቱ ላይ የሚኖረውን አመኔታ የበለጠ ይሸረሽራል የሚል ስጋት አለን።

በትግራይ፣ አማራ እና አፋር ክልሎች የሰሜኑ ጦርነቱ የቆመ ቢሆንም፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች

በውጭ ኃይሎች ጭምር እንደሚፈፀሙ መረጃዎች እየወጡ ነው። ጦርነቱ መቆሙን ተከትሎ በትኩሱ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ምርመራ እና የማሰባሰብ ስራ ስለመካሄዱ ምንም ፍንጭ አለመኖሩ ፣ ማስረጃ በወቅቱ መሰብሰብ እና የመብት ጥሰት ፈፃሚዎችን በሽግግር ፍትህ ስርዓት ተጠያቂ ለማድረግ የሚደርገውን ጥረት እንዳይገድበው ያሰጋል።

ከዚህ በተጨማሪም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተጠርጣሪ ዜጎችን ፍርድ ቤት ማቅረብ የተከለከለ ይመስል፡ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች፣ የሚዲያ ሰዎች፣ የፌደራል እና የክልል ተወካዮች ምክር ቤት አባላት እና የሚኒስትር ዲኤታ ማዕረግ ያላቸው ኃላፊ ጭምር ያለመከሰስ መብታቸው ሳይነሳ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለረዥም ጊዜ መታሰራቸውን ታዝበናል። ከዚህም አልፎ፣ ተጠርጣሪዎቹ የሚታሰሩበት ቦታ መደበኛ ማረሚያ ቤት ወይም ለዚሁ የተዘጋጀ የጊዜ ቀጠሮ ተጠርጣሪዎች ማቆያ ቦታ ሳይሆን ሐሩርና ንዳድ የበዛበት ወታደራዊ ማሰልጠኛ መሆኑ፣ ዜጎች ጉዳዩን የህግ ማስከበር ሳይሆን የበቀል አድርገው እንዲያዩት የሚጋብዝ፣ በመሆኑም በገለልተኛ የፍትህ ሂደት ላይ ህዝብ ያለውን ዕምነትና ተስፋ የሚያቀጭጭ ነው። ይህ ደግሞ ለሽግግር ፍትህ ተግባራዊነት ወሳኝ የሆነውን

2

የህዝብ አመኔታ እና ቅቡልነት ይጎዳል። ስለሆነም መንግስት ባፋጣኝ የማስተካከያ ዕርምጃ በመውሰድ፣ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የሚታሰሩ ዜጎች በመደበኛው የፍርድ ሂደት ጉዳያቸው የሚታይበት፣ ወደ መደበኛ ማረፊያ ቤቶች ተዛውረው፣ ጠበቃ እና ቤተሰብ የማግኘት መብቶቻቸው በግልጽ ችሎት ፍርድ የሚያገኙበት እና ፍትሃዊ ፍርድ የሚያገኙበት አሰራር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል።

ከላይ እንደጠቀስነው የሽግግር ፍትህን በማሳለጥ ረገድ ዋነኛው ኃላፊነት የመንግስት ቢሆንም፣ የታጠቁ ቡድኖችም አንዳንድ አባሎቻቸው በየጊዜው በህዝብ ላይ የሚፈፅሙትን ሰቆቃ እና የመብት ጥሰት አስቁመው፣ ለሰላማዊ የፖለቲካ ድርድር ዝግጁ በመሆን፣ በትግራይ እንደታየው ሁሉ በኦሮሚያና አማራ ክልሎችም ግጭቶች እንዲቆሙ፣ ህዝብ እፎይታ እንዲያገኝ፣ ተጠያቂነትን ዕርቅን ያማከለ የሽግግር ፍትህ ሂደት እንዲኖር የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል። ይህ ካልተደረገ፣ በሃገሪቱ ዘላቂ ሰላምን፣ ብሔራዊ ምክክርንም ሆነ የሽግግር ፍትህን ተግባራዊ ማድረግ በእጅጉ አስቸጋሪ እንደሚሆን በአፅንኦት ለመግለፅ እንወዳለን።

4. <u>በሽግግር ፍትህ ሂደት አግባብነት ያላቸው ተቋማት ሚና በፖሊሲው ውስጥ ሊካተት የሚገባ መሆኑ</u> <u>ሀ. የሃገራዊ ምክክር ኮሚሽኑን ሚና በተመለከተ</u>


በሃገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 1265/2014 አንቀፅ 6 መሠረት የኮሚሽኑ ዓላማ በተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎች፣ እንዲሁም በመንግስት እና በህዝብ መካከል ያለውን

ግንኙነት በማሻሻል ሰላምና መተማመን የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲገነባ ማስቻል፣ ለዚህም ለዘመናት የቆዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መግባባት እና የዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ ባህል ማጎልበት ነው። በሌላ በኩል የሽግግር ፖሊሲው ዋነኛ ዓላማ የተቀናጀ የሽግግር ፍትህ ሂደት የሚመራበት ስርዓት በመዘርጋት ዘላቂ ሰላም፣ ዕርቅ፣ የህግ የበላይነት፣ ፍትህ እና ዲሞክራሲ የሚረጋገጥበትን መደላድል መፍጠር ነው። ስለሆነም፣ የሽግግር ፖሊሲው ዓላማ የሃገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ከሚያከናውነው ቁልፍ ተግባር ጋር በእጅጉ የተሰናሰለ ነው።

ከአዋጁና ረቂቅ ፖሊሲ ማብራሪያው ለመረዳት እንደሚቻለው፣ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲውም ሆነ የሃገራዊ ምክክር ሂደቱ ዓላማና ግብ በእጅጉ ተመሳሳይ፣ ቁርሾና አለመተማመንን በማጥፋት ሰላምና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ሃገርን መፍጠር ላይ ያተኮረ ነው። በመሆኑም፣ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ የሚከናወንበት ህጋዊና ፖለቲካዊ ማዕቀፍ፣ ከሃገራዊ ምክክር ሂደቱ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ስለሆነ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊነታቸውን ማረጋገጥ የዓላማና ተግባር መደራረብ እና ብዥታ እንዳይኖርም ማጥራት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ በዝርዝር ተግባራት (በተለይ የእውነት ማፈላለግና ማካካሻ ተግባራትን በተመለከተ) ከሐገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ስራዎች ጋር የሚቀናጁበትን እና በጊዜ ሰሌዳም ሆነ በአፈጻፀም የሚደጋገፉበትን፣ ድግግሞሽም የሚቀርበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል። የሽግግር ፍትህ ስራዎችን የሚያከናውኑ ተቋማት ከሃገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩበትን ሁኔታ፣ እንዲሁም በፅንሰ ሐሳብና ዓላማ ደረጃ በሽግግር ፍትህ እና በሃገራዊ ምክክር ስራዎች መካከል ያለው ግንኙነት በፖሊሲው ውስጥ ተብራርቶ ቢቀመጥ በዜጎች ዘንድ የሚፈጠርን ብዥታ ለማጥራት፣ ስራውንም በተሻለ ሁኔታ ለማከናወን ይበጃል።

ለ. <u>የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የዕንባ ጠባቂ ተቋምን ሚና በተመለከተ</u>

በተመሳሳይ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የሰብዓዊ መብትና ዲሞክራሲያዊ ባህልን ከማስፋፋት በተጨማሪ፣ የመብት ጥሰት ፈፃሚዎችም ተጠያቂ እንዲሆኑ የመታገል ተልዕኮ ያለው መንግስታዊ ተቋም ነው። የሽግግር ፍትህ ስራውም ተጠያቂነትን በማረጋገጥ እና ለዲሞክራሲ መደላድል በመፍጠር ረገድ ከኮሚሽኑ ተልዕኮ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ስለሆነም በሽግግር ፍትህ ተቋማት እና በሰብዓዊ መብት ኮሚሽኑ መካከል የሚኖረው ቅንጅት እና የስራ ግንኙነት ዘርዘር ብሎ በፖሊሲው ላይ ቢቀመጥ የተሻለ ነው። የዕንባ ጠባቂ ተቋምም ቢሆን3



ዜጎች ላይ የሚፈፀሙ አስተዳደራዊ ጥሰቶችና በደሎች በመለየት መፍትሄ የማመላከት ተልዕኮ ያለው በመሆኑ ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ በእጅጉ ቅርብ ነው።

እነዚህ ተቋማት ለሽግግር ፍትህ፣ በተለይም ለእውነት ማፈላለግ ስራውም ሆነ ለክስ ሂደቱ ያሏቸውን መረጃዎችና ማስረጃዎች ለሽግግር ፍትህ ተቋማቱ ከማጋራት ጀምሮ፣ ስለሽግግር ፍትህ እና ሰብዓዊ መብቶች በህዝቡ ዘንድ የተሻለ ግንዛቤ እንዲዳብር፣ የመብት ጥሰቶችን

የሚመለከቱ መረጃዎች በአግባቡ እንዲሰነዱ በማድረግ (documentation)፣ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን በመጠቀም የህብረተሰቡን የሰብዓዊ መብትና ህግ ንቃተ ህሊና በማሳደግ፣ በሽግግር ፍትህ ዳኝነት ሂደት ለሚሳተፉ ዳኞችና ዓቃብያነ ህግ ስልጠና በመስጠት፣ በሽግግር ፍትህ የዳኝነት ሂደቶች ምክረ ሃሳቦችና አስተያየቶችን በማቅረብ፣ በየጊዜው የፍርድ፣ ዕውነት የማፈላለግ እና የካሳ ስራዎች፣ እንዲሁም በዚሁ ሂደት ስራ ላይ የሚውሉ የሃገር በቀል የግጭት አፈታት ተግባራት ከሰብዓዊ መብት ጥበቃ አንፃር በአግባቡ መከናወናቸውን መከታተልና መገምገም፣ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ አተገባበር የተሻለ እንዲሆን ምክርና ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት፣ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላም የፍርድ እና የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽኑን ሰነዶች ጠብቆ በማስቀመጥ እና ወደፊት ለጥናት፣ ምርምር እና ማስተማሪያነት በማዋል ረገድ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽኑ ጉልህ ድርሻ ስላለው ይኸው በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ በአግባቡ ሊገለጽ ይገባል።

ሐ. <u>የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ሚና በተመለከተ</u>

በሽግግር ፖሊሲ ማብራሪያው ላይ የሲቪል ማኅበረስብ ድርጅቶች ዕውቅና ተሰጥቷቸው ሚናቸው መገለጹ በጎ ጅምር ነው። በዚህ ረገድ የሲቪል ማኅበረብ ድርጅቶች ህብረተሰቡ ስለ ሽግግር ፍትህ ያለውን ግንዛቤ በማሳደግ፣ ሂደቱን በፋይናንስ፣ በቴክኒክ እና በሌሎች መንገዶች በመደገፍ እንዲሁም በአተገባበር ወቅት በቀጥታ በመሳተፍ እና የሂደቱን ውስን ክፍሎች በሙሉ ኃላፊነት እንዲተገብሩ በማድረግ እንደሚሳተፉ መገለፁ በእጅጉ የሚበረታታ ነው። ነገር ግን የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሚና እንደ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽኑ ሁሉ ከዚህም ሊያልፍ ይገባል የሚል ዕምነት አለን። በዚህ ረገድ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በሽግግር ፍትህ የዳኝነት ሂደቶች ምክረ ሃሳቦችና አስተያየቶችን በማቅረብ፣ በእጃቸው የሚገኙ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መረጃዎችና ምርመራ ውጤቶችን ለሽግግር ፍትህ ተቋማት ማጋራት፣ የሽግግር ፍርድ ሂደቶችን መከታተል (trial monitoring) ጨምሮ የሽግግር ፍትህንም ሆነ እውነት አፈላላጊ ኮሚሽንን ስራዎች፣ እንዲሁም በዚሁ ሂደት ስራ ላይ የሚውሉ የሃገር በቀል የግጭት አፈታት ተግባራት ከሰብዓዊ መብት ጥበቃ እና ተጠያቂነት አንፃር በአግባቡ መከናወናቸውን መከታተልና መገምገም፣ ቀደም ሲል በደርግ ወታደራዊ አገዛዝ ወቅት የተፈፀሙ ወንጀሎችን ለመመርመር እና ለፍርድ ለማቅረብ የተሰራውን ስራ መለስ ብሎ በመገምገም ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ ጠቃሚ ልምዶችንና ትምህርቶችን መለየት፣ እንዲሁም ከሽግግር ፍትህ ጋር የተያያዙ የጥናትና ምርምር ስራዎች ላይ እንዲሁም በአጠቃላይ በሽግግር ፍትህ ስርዓቱ አፈፃጸም ላይ የክትትልና ግምገማ ስራ ላይ በመሳተፍ ሂደቱን ሊደግፉ ይችላሉ። ይህም በፖሊሲው ላይ ዘርዘር ብሎ ቢቀመጥ፣ የሽግግር ፍትህን የሚተገብሩ ተቋማት እና አግባብነት ያላቸው ባለድርሻ አካላት ስለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አጋርነት ያላቸውን ግንዛቤ ለማዳበርና ስራውንም ለማሳለጥ ያግዛል።

<u>መ. የመገናኛ ብዙኃን፣ ሃይማኖት ተቋማት እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሚናን በተመለከተ</u>

የመገናኛ ብዙኃን እና የሃይማኖት ተቋማት ህብረተሰቡ ስለሽግግር ፍትህ ያለውን ግንዛቤ እና አዎንታዊ አመለካከት በማሳደግ፣ ለቅቡልነቱ፣ ሆነም ለስኬቱ ያላቸው አስተዋፅኦ የማይናቅ ነው። ከዚህ ባለፈም የመገናኛ ብዙኃን፣ የማኅበራዊ ሚዲያ ዘዋሪዎችን ጨምሮ ከጥላቻ ንግግሮች በመቆጠብ እና መቻቻል እና ደርዝ ያለው ውይይትን በማዳበር ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ ከፍ ያለ ሚና አላቸው። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም በሽግግር ፍትህ ሂደት የአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች፣ የሰብዓዊነት እና የወንጀል ህጎች በኢትዮጵያ ህግ ማዕቀፍ በሚተገበሩበት እና በሚተረጎሙበት ሁኔታ ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ በዘርፉ ለሚኖረው ስነህግ መዳበር







ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ። የፖለቲካ ማኅበረሰብ ሳይንስ ምሁራንም እንዲሁ የእውነት ማፈላለግ እና ዕርቅ ሂደቶች ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት እና ማኅበረሰባዊ መተማመን የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ እንዲሁም ይህንኑ ለማጎልበት በሂደቱ ሊወሰዱ የሚገባቸውን ዕርምጃዎች በተመለከተ በጥናት የተደገፈ ግብዓት በማቅረብ ይረዳሉ። ስለሆነም የመገናኛ ብዙኃን፣ የሃይማኖት ተቋማት እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሽግግር ፖሊሲው ሂደት የሚኖራቸው ሚና በፖሊሲው ውስጥ ሊጠቀስ ይገባል።

5. <u>የተፈፃሚነት ወሰንን በተመለከተ</u>

የረቂቅ ፖሊሲው ማብራሪያ ሰነድ፣ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ተፈጻሚ የሚሆነው በመላ ሃገሪቱ እንደሆነ ይገልጻል። ይሁንና፣ በትግራይ ክልል በነበረው ጦርነት፣ የኤርትራ ወታደሮች በከባድ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት እና የጦር ወንጀል ተሳትፎ እንደነበራቸው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች ዋና ኮሚሽነር አረጋግጠዋል፣ ይህም በተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነሮች ጭምር ተረጋግጧል። ስለሆነም፣ በጦር ወንጀል እና ከባድ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የተሳተፉ የኤርትራ ወታደሮች ጉዳይ በሌሉበትም ቢሆን በሚቋቋመው ልዩ ፍርድ ቤት ሊታይ እና ተጠያቂነታቸውም ሊረጋገጥ፣ በእውነት አፈላላጊ ኮሚሽኑ አማካኝነትም በነዚሁ የውጭ ኃይሎች የተፈፀሙ ከባድ ወንጀሎች ይፋ ሊደረጉ፣ እውነቱ ሊታወቅ እና ሊሰነድ ይገባል። በዚህ ረገድ ጉዳዩን የሚያየው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ከባድ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በተፈጸሙ ጊዜ በሌሎች ሃገሮችም እንደሚደረገው ሁሉንዓቀፍ የዳኝነት ስልጣን (universal jurisdiction) እንዲኖረው የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ሊዘጋጅ ይገባል።

6. <u>የሽግግር ፍትህ የሚመሩባቸው መርሆዎች</u>


በማብራሪያው ላይ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ የሚመራባቸው መርሆዎች፣ (ማለትም ሰብዓዊ መብት ተኮር ትግበራ፣ ማንንም አለመጉዳት፣ ሃገራዊ ባለቤትነት፣ አውድ ተኮር አተገባበር፣ ተጠያቂነት፣ ሁለንተናዊነት፣ አካታችነትና አሳታፊነት፣ ስርዓተ ፆታ ተኮር አተገባበር፣ ሃገር በቀል የግጭት አፈታት ዕሴቶችን ጥቅም ላይ ማዋል) በዝርዝር የተመለከቱ ሲሆን ስማችን በዚህ አስተያየት ላይ የተጠቀሰው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ የምንደግፋቸው ናቸው። በተጨማሪም በማብራሪያው ላይ የሽግግር ፖሊሲ አላማና አፈጻጸምን በተመለከተ በዝርዝር የተመለከቱት ጉዳዮች በእኛ አስተያየት አለምዓቀፍ የሰብዓዊ መብት መርሆዎችን የተከተሉ እና አካታች ሆነው አግኝተናቸዋል። የፖሊሲው ዝግጅት ቀደም ሲል የጥናት ቡድኑ ያካሄደውን እና የኢሰመኮ እና የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች ዋና ኮሚሽነር ምክረ ሃሳቦችን መሠረት ያደረገ፣ ከዚህ በታች የምናነሳቸው አስተያየቶች እንደተጠበቁ ሆነው በጥሩ ሁኔታ የተሰራ እንደሆነ ከማብራሪያ ሰነዱ እና ከተደረገው ገለጻ መረዳት ችለናል።

ሃገር በቀል የግጭት አፈታት ዕሴቶችን ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ በፖሊሲ ማብራሪያው ላይ የተቀመጠውን የምንደግፈው ቢሆንም፣ በተለይ በክልሎችና ወረዳዎች በሚፈፀምበት ወቅት ሰብዓዊ መብቶች ያማከለ እና የተጎጂዎችን፣ በተለይም የሴቶችን፣ ህፃናትንና አካል ጉዳተኞችን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ተግባራዊ እንዲደረጉ ልዩ ትኩረትና ክትትል ሊሰጥ ይገባል። በዚህ ረገድ ኢሰመኮ እና የሲቪል ማኅበረሰብ ተቋማት ግንባር ቀደም ሚና እንደሚኖራቸው እናምናለን።

7. የወንጀሎች አተረጓጎምና ተጠያቂነትን በተመለከተ

በፖሊሲ ማብራሪያው ላይ በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ለፍርድ የሚቀርቡት በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ የነበራቸው ግለሰቦች እንደሆኑ ተጠቅሷል። በዚህ አካሄድ መሠረተ ሃሳብ እና በምክንያቱም የምንስማማ ቢሆንም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና ምን ምንን እንደሚያካትት

5



በተቻለ መጠን ግልፅና የማያሻማ በሆነ መንገድ መካተት ይኖርበታል። በዚህ ረገድ ወንጀሎቹ አስገድዶ መድፈርን፣ የሲቪል ንብረትና አገልግሎት ተቋማትን፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ቅርሶችን ማውደምን ጨምሮ ዓለማቀፍ የሰብዓዊነት ህግ (international humanitarian law) በመጣስ የሚፈፀሙ የጦር ወንጀሎችን፣ ግዙፍ እና መልክ ይዘው የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን፣ ዘር ማጥፋት እና በሰብዓዊነት ላይ የሚፈፀም ወንጀልን፣ ከበባ እና ማስራብን (siege) እንደጦርነት ስልት መጠቀምን ጨምሮ ሌሎች ተፈፅመዋል በሚል ስሞታ (allegation) የቀረበባቸውን ወንጀሎች ሊያካትቱ ይገባል። በተለይም በሰብዓዊነት ላይ የሚፈፀም ወንጀል በኢትዮጵያ ህግ ያልተካተተ በመሆኑ፣ የአለም አቀፍ ህግ ድንጋጌዎችና ልምድን መሠረት በማድረግ ሊበየን ይገባል።

የተሳትፎ ደረጃን በተመለከተም፣ የወንጀል ድርጊቶቹን ማቀድ፣ ማዘዝ እና በቀጥታ መተግበር ብቻ ሳይሆን፣ ሆን ብሎ ግዴታን ባለመወጣት ህዝብን ለጥቃት ማጋለጥ፣ ለወንጀል ፈፃሚዎች መረጃ በመስጠት፣ ወይም ለተጠቂዎች መረጃ ባለመስጠት እና ጥበቃ ባለማድረግ መተባበር፣ እንዲሁም ስልጣንን መከታ በማድረግ ወንጀል ፈፃሚዎች እንዳይቀጡ ወይም ከፍትህ እንዲያመልጡ መርዳት ጭምር እንደየደረጃው በሽግግር ሂደቱ በወንጀል የሚያስጠይቅ ሊሆን ይገባል። ይህም መንግስት በሁሉም ደረጃ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ መሆኑን ባለስልጣናትና ኃላፊዎችም ስልጣናቸውንና ብሄራቸውን ከለላ በማድረግ ከተጠያቂነት እንደማያመልጡ ለማሳየት ይረዳል።

8. <u>የልዩ ዓቃቤ ሕግ ተቋምን በተመለከተ</u>


በማብራሪያው ላይ እንደተጠቀሰው፣ ሞያዊ ብቃትን፣ ገለልተኝነትና ህዝባዊ አመኔታን ለማረጋገጥ በሽግግር ፍትህ ወንጀሎችን የማጣራት እና ክስ የማቅረብ ስራ በልዩ ዓቃቤ ህግ እንዲመራ መደረጉ የሚደገፍ ነው። በዚህ ረገድ ክስ በመመስረት ብቻ ሳይሆን፣ የወንጀል ምርመራን የሰብዓዊ መብቶችን ባከበረ መንገድ ለማከናወን እንዲቻል የልዩ ዐቃቤ ህግ ተቋሙ በቂ ስልጠና እና ልምድ ያገኙ ፖሊሶች ሊኖሩት እና የወንጀል ምርመራውን እና ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር የማዋል ስራውን የሚያከናውን የፖሊስ ክፍል በስሩ ሊደራጅ ይገባል።



ምርመራና ክስን በተመለከተ፣ ወንጀሎቹ አለም ዓቀፋዊ ባህርይ ያላቸውና ልዩ ሙያ እና ዕውቀትን የሚጠይቁ በመሆኑ፣ ለባለሙያዎች ከሚሰጥ ስልጠና በተጨማሪ በጉዳዩ ሰፊ ልምድና ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎች በአማካሪነት እና ከፍተኛ ዓቃቤ ህግነት ቢሳተፉ ስራው የሚጠይቀውን ዕውቀትና ክህሎት ለማሟላት፣ የዕውቀት ሽግግር ለማድረግና ሂደቱም ቅቡልነት እንዲኖረው ይረዳል።



በምርመራን እና ክስ ሂደት፣ በተለይ ሴቶች ላይ የተፈፀሙ ጥቃቶችና ወንጀሎችን በሚመለከት፣ በተጎጂዎች እምነት እንዲጣልባቸው እና ጉዳዩንም በአግባቡ ለመረዳት ብቃት ያላቸው ሴት ባለሙያዎች ቢመደቡ መልካም ይሆናል።

9. <u>ልዩ ፍርድ ቤትን በተመለከተ</u>

በፖሊሲ ማብራሪያው ላይ የሽግግር ፍትህ ጉዳዮች የሚታዩት በልዩ ፍርድ ቤት መሆኑ ተገልጧል። ልዩ ፍርድ ቤትን ለማቋቋም በማብራሪያው ላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች አሳማኝ ቢሆኑም የልዩ ፍርድ ቤት ህገመንግስታዊነት በአግባቡ ሊታይ ይገባል። በዚህ ረገድ "የዳኝነት ስልጣንን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጥዕው ተቋም ውጭ የሚያደርግ፣ በህግ የተደነገገን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ፍርድ ቤት ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም።" የሚለውን የኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 78(6)
መሠረት በማድረግ ልዩ ፍርድ ቤት ህገመንግስታዊ አይሆንም የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል። በዚህ ረገድ የህገመንግስቱ አንቀፅ ሊታይ የሚገባው ከመነሻው እና ድንጋጌው ከወጣበት አውድ አንፃር ነው የሚል ዕምነት6



አለን። በህገ መንግስቱ ልዩ ፍርድ ቤት ለመከልከል መነሻ የሆነው፣ በደርግ ወታደራዊ አገዛዝ በህግ ባልተቋቋሙ፣ ህጋዊ የፍርድ ስርዓትን ባልተከተሉ እና የዳኞቻቸውም ማንነት በማይታወቅ "ልዩ ፍርድ ቤቶች" የዜጎች ህይወት ሲቀጠፍ፣ ለዓመታት እስራትና ስቃይ ሲዳረጉ መቆየታቸው ነው።

ስለሆነም የህገመንግስቱ ዓላማ በህግ ያልተቋቋሙ፣ ተጠያቂ ያልሆኑ እና ፍትሃዊ የፍርድ ሂደት መርሆዎችን (fair trial standards) የማይከተሉ አካላትን ለመከልከል እንጂ፣ በህግ የተቋቋመን፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት እና ፍትሓዊ የፍርድ ሂደት መርሆዎችን ያሟላን፣ በግልፅ የሚያስችል እና ዳኞቹም በህግ አግባብ የተሾሙ የዳኝነት ተቋምን ለመከልከል አይደለም። ስለሆነም እነዚህን ሁኔታዎች እስካሟላ ድረስ በሽግግር ፍትህ ሂደት የሚቋቋመው ልዩ ፍርድ ቤት ኢህገመንግስታዊ ነው ሊባል አይችልም። እንዲያም ሆኖ ልዩ ፍርድ ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች የሚኖሩት እንዲሆን፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱም የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ልክ እንደሰበር ሰሚ ችሎት ሁሉ እነዚህን ጉዳዮች በሚመለከት ገዢ እንዲሆኑ ቢደረግ በዘርፉ ለስነህግ መዳበር አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በሁለቱም ደረጃ ባሉ ችሎቶችም ከኢትዮጵያውያን በተጨማሪ፣

የጦር ወንጀሎችን ጨምሮ ዓለማቀፍ ወንጀሎችና ከባድ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በመዳኘት ዕውቀትና ልምድ ያላቸው የውጭ ሃገር ባለሙያዎች በዳኝነት ቢመደቡ ለፍትህ ሂደቱ ቅቡልነት፣ ለውሳኔዎች ጥራት፣ ለዕውቀት ሽግግር እና በዘርፉ ለስነ ህግ ዕድገት ተመራጭ ይሆናል። እነዚህ የውጭ ሃገር ባለሙያዎች በዳኝነት ከመሰማራታቸው በፊት፣ በኢትዮጵያ ህግ ስርዓት እና የስነስርዓት ህጎች እንዲሁም ድርጊቶቹ በተፈፀሙበት አውድ ዙሪያ በቂ ስልጠና እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል።

10. <u>በፍርድ ሂደት የሲቪል ማኅኅበረሰብ ድርጅቶችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ሚና በተመለከተ</u>


ከላይ እንደጠቀስነው፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና የህግና ሰብዓዊ መብት ትምህርት ቤቶች የፍርድ ሂደቱን በመታዘብ፣ እንዲሁም የህጎችን አተረጓጎም በሚመለከተ ለዳኝነት አካላት አስተያየት (amicus curiae) በማቅረብ፣ በፍርድ ቤቱ በሚሰጡ ፍርዶች ላይ የጥናትና ምርምር ስራዎችን እንዲሁም የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት በሂደቱ ሊሳተፉ ይገባል። ከዚህ ባለፈም ዳኞችና አቃቢያነ ህግ፣ እንዲሁም የእውነት አፈላላጊ እና ዕርቅ አካላት የሌሎች ሃገራትን የሽግግር ፍትህ አሰራር በተመለከተ ልምድ የሚቀስሙባቸው መድረኮች እና የጉብኝት ፕሮግራሞች የሃገር ውስጥና የውጭ የሲቪል ማኅበረሰብ ተቋማት ሊያዘጋጁ ይችላሉ።

ከዚህ በተጨማሪም፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በሽግግር ፍትህ ስርዓቱ በወንጀል በተፈረደባቸውን ግለሰቦች እና ተጠያቂነታቸው የተረጋገጠባቸውን ተቋማት አይ ተብዳዮች ካሳ እንዲያገኙ የፍትሐብሔር ክስ መስረተው እንዲከራከሩ፣ የህክምና የሞያ ማኅበራትም ህክምና ነክ ማስረጃዎችን (forensic evidence) በማደራጀት እና በማቅረብ እንዲሳተፉ ሊበረታቱ ይገባል።

11. <u>ለሽግግር ፍትህ አስፈላጊ የሆኑ የህግ ማሻሻያዎችን በተመለከተ</u>

ከላይ እንደተገለፀው፣ የሽግግር ፍትህ ሂደት በዓይነቱ የተለየ እና ሁሉን አቀፍ በመሆኑ፣ ይህንኑ የሚመጥን የህግ ማሻሻያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል። በዚህ ረገድ በተለይ የአለም አቀፍ የወንጀል እና የሰብዓዊ መብት ህጎችን መሠረት ያደረገ እና በዚህ አግባብም አዳዲስ የወንጀል ርዕሶችን ያካተተ የወንጀል ህግ ማሻሻያ ያስፈልጋል። የወንጀል ስነስርዓትን በተመለከተም፣ አዲስ የተረቀቀው የተሻሻለ የወንጀል ስነስርዓት ህግ መፅደቁ እንዳለ ሆኖ፣ በአለም አቀፍ ደረጃ ተመሳሳይ የዳኝነት ሂደቶች የሚመሩበትን ስርዓት በተከተለ መልኩ ልዩ የምርመራ እና የወንጀል ዳኝነት ስነስርዓት መከተል ያስፈልግ እንደሆነ ለማረጋገጥ በቂ ጥናት ሊደረግ ይገባል።





የእውነት ማፈላለግ፣ የማካካሻ፣ የማገገሚያ እና የዕርቅ ስርዓቶችም ህጋዊ አሰራር ሊበጅላቸው የሚገባ ሲሆን፣ ሃገር በቀል የግጭት አፈታት ስርዓቶች በሽግግር ፍትህ ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉበት፣ በዚህ ረገድም ባህላዊ ህጎችን በዘመናዊ የህግ ስርዓት ውስጥ በማካተት ፈር ቀዳጅ የሆነ የህግ ማሻሻያ ቢደረግ መልካም ይሆናል።

በመጨረሻም፣ የሽግግር ፍትህ ሂደቱን ለጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ አድልዎ፣ ስርዓተ አልበኝነት፣ ብሄር፣ ፆታ እና ሃይማኖት ተኮር ጥቃት እንዲሁም ቅጥ ያጣ በስልጣን መባለግ በር የከፈቱ ህጎችና አሰራሮችን፣ ተቋማዊ ክፍተቶችና ጉድለቶችን ለመለየት እና የተሟላ የህግ እና ተቋማዊ ማሻሻያ ለማድረግ መንግስት እና ባለድርሻ አካላት ሊጠቀሙበት ይገባል።

12. <u>ማጠቃለያ</u>

ከላይ እንደገለፅነው፣ በሽግግር ፍትህ አማራጮች ላይ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያሳተፉ በርካታ ውይይቶች መደረጋቸው፣ በሂደቱም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽነር መሳተፋቸው፣ ጉዳዩን በተመለከተ የባለሙያዎች ቡድን ተቋቁሞ ጥልቀት ያለው ጥናት መሰራቱ አበረታች እና በሌሎች ወሳኝ የፖሊሲ እና ህግ ማርቀቅ ጉዳዮችም መንግስት ሊተገብረው የሚገባ በጎ ጅምር ነው። ሒደቱ የተሟላና ውጤታማ እንዲሆን፣ ረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲውም ለህዝብ ይፋ ሆኖ ባለድርሻ አካላት የተደራጀ አስተያየት ሊያቀርቡበት ይገባል።

ከግልፅነት እና ተሳትፎ ጉዳዮች በተጨማሪ፣ አገራችን የምትገኝበት አሳሳቢ የፀጥታ ሁኔታ እና የተጠያቂነት ዕጦት ካልተስተካከለ፣ ብዙ የተለፋበትን የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ለመተግበር እጅግ አስቸጋሪ ያደርገዋል። በፖሊሲው ይዘት ላይ ካቀረብናቸው አስተያየቶች በተጨማሪ፣ የሽግግር ፍትህ ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር በቅንጅት እና በትብብር መተግበር ያለበት ሲሆን፣ በዚህ ረገድ የተቋማቱ ድርሻ በፖሊሲው ቢመለከት ለስራው ውጤታማነት ይረዳል፣ የተሻለ ተጠያቂነትንም ለማረጋገጥ ያስችላል። ብዥታን ለማጥራትም የሽግግር ፍትህ እና ሃገራዊ ምክክር ያላቸው ቁርኝትና የአፈፃፀም ተደጋጋፊነት በፖሊሲው ሊገለፅ ይገባል። በመጨረሻም፣ ከላይ ያቀረብናቸውን አስተያየቶች መንግስት የምር በመውሰድ ለሽግግር ፍትህና ተጠያቂነት ያለውን ቁርጠኝነት እንዲያሳይ እንጠይቃለን።

1. ሰብዓዊ መብቶችና ዲሞክራሲ አራማጅ ማዕከል (CARD)
2. የሕግ ባለሙያዎች ለሰብዓዊ መብቶች (LHR)፣
3. የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (NEWA)፣
4. ሴታዊት
5. የኢትዮጵያ ሠራተኞች መብት ተሟጋች (ELRW)፣
6. ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ (AHRE)፣
7. ሁሉን አቀፍ ራዕይ ለዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ (IVIDE)፣
8. የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ማዕከል (EHRDC)